የሰበር መ/ቁ. 18399

28/09/98

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

" ዓብዱልቃድር መሐመድ

" ጌታቸው ምህረቱ

" መስፍን እቁበዮናስ

ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት

ተጠሪዎች፡- እነ ትዕግሥት ብዙነህ (6 ሰዎች)

## ፍ ር ድ

ይህ የሠበር አቤቱታ የቀረበው የአሁኑ አመልካች በስር ፍ/ቤት ለቀረበበት ክስ መልስ ይዞ እንዲቀርብ በተቀጠረው ቀን ቀጠሮ ባለመቅረቡ ከክሱ ውጪ እንዲሆን የተሰጠውን ትእዛዝ በመቃወም ነው።

የአሁኑ ተጠሪዎች በአመልካች እና በሌሎች ሁለት ተከሣሾች ላይ ላቀረቡት ክስ አመልካች መልስ እንዲሰጥ ታዞ በቀን ቀጠሮው ባለመቅረቡ ከክሱ ውጪ እንዲሆን ታዟል። ከዚህ በኋላም ቢሆን አመልካች ትእዛዙ ተነስቶ ወደ ክርክሩ እንዲገባ ያቀረበውን ጥያቄ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ሳይቀበለው ቀርቷል። በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሠረት ሠርዞታል።

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ሲሆን ተጠሪዎች ቀርበው ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን የጽሁፍ ክርክር መርምሯል። በዚህም ጉዳይ ሊነሣ የሚገባው የሕግ ነጥብ መልስ እንዲቀርብ በተያዘ ቀን ቀጠሮ የተከሣሽ አለመቅረብ የሚያስከትለው ውጤት ምድነው? የሚለው ነው።

ከላይ የተያዘው ጭብጥ ለመመለስም ባለጉዳዩ ወደ ፍ/ቤት ሳይቀርብ መቅረቱ የሚያስከትለውን ውጤት የሚደነግጉትን የፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ ድንጋጌዎች መመልከት ጠቃሚ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ___ ቀን 28-10-98

ነው በተለይ አንድ ባለጉዳይ ከክሱ ውጪ እንዲሆን የሚደረገው በየትኛው የሙግት ደረጃ ላይ ፍ/ቤት ባይቀርብ ነው የሚለው መታየት አለበት፡፡

በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 70(ሀ) መሠረት ተከሣሽ ከክሱ ውጪ (ex-parte) የሚሆነው ክርክሩ እንዲሰማ በተወሰነው ቀኑ-ቀጠሮ ያልቀረበ እንደሆነ ነው እንጂ መልስ እንዲያቀርብ በተያዘው ቀነ ቀጠሮ ባለመቅረቡ አይደለም መልስ እንዲቀርብ በተያዘው ቀነ ቀጠሮ አለመቅረቡ የሚያስከትለው ውጤት ጉዳዩ ተከሣሽ ባይቀርብም በሌለበት መቀጠል (default proceeding) ብቻ መሆኑን ከፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 233 መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከፍ ሲል የተጠቀሱት አንቀፆችም በመ/ቁ. 15835 ትርጉም ተሰጥቶባቸዋል፡፡

በመሆኑም አመልካች መልስ እንዲያቀርብ በተያዘው ቀነ ቀጠሮ ባለመቅረቡ ከክሱ ውጪ እንዲሆን የተደረገው ከሥነ ሥርዓት ሕጉ ውጪ ነው፡፡

## ው ሣ ኔ

1/የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ.15610 በ4/02/97 የሰጠው ትእዛዝ እንዲሁም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 34885 በ12/04/97 የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡

2/ የአሁኑ አመልካች በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በሚደረገው ክርክር ከክርክሩ ውጪ ሊሆን ስለማይገባ መልሱን ባያቀርብም ወደ ክርክሩ ገብቶ ፍ/ቤቱ ክሱን ከሰማ በኋላ የመሠለውን ይወስን፡፡

3/ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ መዝገቡ ስለተዘጋ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ___ ቀን 28-10-98